# የተወዳጁ የወንጌል ሰባኪ እና አስተማሪ፤ ጠንቃቃውና ትጉ የቤ/ክ መሪ
# የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ አጭር የሕይወት እና የአገልግሎት ታሪክ

## የትውልድ ዘመንና የትምህርት ዓለም

ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ከአባታቸው ከአስር አለቃ ሀብቴ ወ/ማርያም እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘነበች ወልዴ ጥር 8 ቀን 1944 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ በቅሎ ቤት አካባቢ ተወለዱ።

እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በንፋስ ስልክ ስብስቴ ነጋሲ ከጨረሱ በኋላ ነጻ የትምህርት ዕድል አግኝተው በጀነራል ዊንጌት ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ በማጠናቀቅ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሽልማት ድርጅት ተሸላሚ ሆነዋል።

ከ1961-1967 የቀድ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲ የሕክምና ፋክልቲ በሕክምና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።

ከ1972-1974 በግላስኮ ስኮትላንድ በኩላሊት ሕክምና ስፔሻላይዝ አድርገዋል። እንዲሁም ከዩኒቨርስቲ ኦፍ ኒው ካስል በክሊኒካል ኤፒዲሞሎጂይ ዲፕሎማ አግኝተዋል።

## የሥራ ዓለም

ከ1968-1970 ዓ/ም በባሌ ጐባ ሆስፒታል በሜዲካል ዳይሬክተርነት
ከ1971-1972 ዓ/ም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በጠቅላላ ሀኪምነት
ከ1974-1987 ዓ/ም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በኩላሊት ህክምና ክፍል ሀኪምነት እና የክፍል ሃላፊነት፤ የውስጥ ደዌ ዘርፍ ሃላፊነት፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህክምና ፋክልቲ ረዳት ፕሮፌሰርነትና ተባባሪ ፕሮፌሰርነት እንዲሁም በህክምና ፋክልቲ ዲን በመሆን በአጠቃላይ በህክምናው መስክ ለ ሃያአንድ ዓመታት አገልግለዋል።

## መንፈሳዊ አገልግሎት

ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ነሐሴ 26 ቀን 1959 ዓ/ም በአስራአምስት ዓመት ዕድሜያቸው የ አስራአንደኛ ክፍል ተማሪ እያሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል መድሃኒታቸው አድርገው ተቀብለዋል። በዩኒቨርስቲው እየተማሩ በነበሩበት ወቅት ለወደፊት ለሚሰማሩበት ሞያ ትምህርት ለመቅሰም ለተጨማሪ ለመንፈሳዊ ህይወታቸውና አገልግሎታቸው ጠንካራ መሰረት ጥለዋል። በዩኒቨርስቲው የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት አርባ ዓመታት በተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ውስጥ ያለምንም መቆጠብ በሙሉ መሰጠት ጌታ ኢየሱስን ሲያመልኩና ሲያገለግሉ ቆይተዋል። በእነዚህም አርባ ዓመታት፡-

- ከ1962-1964 በቅሎ ቤት በምትገኘው የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ በሽማግሌነት

- ከ1968-1970 በባሌ ጐባ ሆስፒታል ተመድበው በሚሰሩበት ወቅት በአካባቢው በነበረው ከፍተኛ የክርስቲያኖች ስደት ምክንያት ቤ/ክርስቲያናት ተዘግተው ስለነበር የዶ/ር ብርሀኑ ቤት የክርስቲያኖች መሰብሰቢያና የወንጌላውያን ማረፊያ ሆኖ ያገለግል ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወንጌላውያን ወህኒ ቤት ሲገቡ ዶ/ር ብርሀኑ ከሌሎች ወገኖች ጋር በመሆን አገልግሎቱ በየቤቱ እንዲቀጥል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ከዚህም የተነሳ የፖለቲካ ድርጅቶችና የመንግስት አካላት ሆነ ብለው ቢከታተሉአቸውም በእጃቸው እንዲወድቁ እግዚአብሔር አልፈቀደም።
-
- በሚያዝያ 1970 ዓ/ም ተቀይረው ወደአዲስ አበባ ከተመለሱ ጊዜ ጀምሮ የብርሃነ ወንጌል ቤ/ክ አባል በመሆን ምሳሌነት ባለው ህይወት በአጥቢያ ቤ/ክ በሽማግሌነት፤ በማስተማርና በመስበክ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል እንዲሁም በብርሃነ ወንጌል ቤ/ክ ታሪክ ውስጥ ቤተክርስቲያኒቱ ተዘግታ እጅግ አስቸጋሪ እና ፈታኝ ስደስ በነበረበት ወቅት ዶ/ር ብርሃኑ ቤተክርስቲያኒቱን ቤት ለቤት ለማደራጀት የተሰየመው አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን የማደራጀቱን ሥራ በመምራት አገልግሎቱ ቀጣይ እንዲሆን ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። እንዲሁም ቤተክርስቲያኒቱን በመወከል ከ1974-1984 ዓ/ም የመጥምቃውያን ወንጌላዊት ማህበር ውስጥ በቦርድ አባልነት ከዚያም አብዛኛውን ጊዜ ሰብሳቢ በመሆን አገልግለዋል።

- ከዚያም ማህበሩን በመወከል ከ1977 ዓ/ም ጀምሮ ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን ሕብረት ለመመስረት እና ለመምራት ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት የኢትዮጵያ ቤ/ክ መሪዎች አንዱ በመሆን አገልግለዋል። በእነዚህም ጊዜያት በስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባልነት፤ በፀሃፊነት፤ በምክትል ሰብሳቢነት እና የሂሳብ ሹም በመሆን እንዲሁም የወንጌል ሥርጭትና ተልእኮ ኰሚሽን ሰብሳቢ በመሆን በጠቅላላው ለአስራአንድ ዓመታት አገልግለዋል። በዚሁ የጊዜ ክልል ውስጥ የወንጌል አማኞች አንድነት ማህበር ፀሃፊ እና ሰብሳቢ በመሆን ለስድስት ዓመታት አገልግለዋል።

- ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ - 19--- የኢትዮጵያ ብርሃነ ወንጌል መጥምቃውያን ቤ/ክ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ከሌሎች የአገልግሎት ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ቤተእምነቱን በማደራጀት እና በመምራት አገልግለዋል።

- እንደዚሁም የባፕቲስት ጀነራል ኮንፍራንስ መንፈሳዊ አገልግሎት ቦርድ ሰብሳቢ በመሆን ለረጅም ዓመታት አገልግለዋል።

- ዶ/ር ብርሃኑ በነበራቸው በሳል የአመራር ችሎታ እና ምሳሌነት ያለው ከፍተኛ ክርስቲያናዊ ሥነምግባር ምክንያት በወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ የአማካሪዎች መማክርት ለአስራስድስት ዓመታት በሁለት የምርጫ ጊዜ ያገለገሉ ሲሆን በዚሁም በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የልማት ለውጥ ለማምጣት ብዙ ጥረዋል። በዚሁም የአማካሪዎቹን መማክርትን ወደቦርድ ደረጃ ለማሳደግ በዓለም አቀፉ ወርልድ ቪዥን ቦርድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። በተጨማሪም ዶ/ር ብርሀኑ የዓለም አቀፉ የወርልድ ቪዥን ቦርድ

አባል ሲሆኑ ለሶስት የምርጫ ጊዜ ተመርጠው ለዘጠኝ ዓመታት አገልግለዋል። ዶ/ር ብርሀኑ በወርልድ ቪዥን በዓለም አቀፍ ቦርድ እጅግ ተወዳጅ እና የተከበሩ እጅግም የላቀ አስተዋፅኦ ያደረጉ ነበሩ።

- ዶ/ር ብርሃኑ በተጨማሪም በደወል የወንጌል አገልግሎት፤ በቃለእግዚአብሔር አንባቢያን ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን እና በሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶች ውስጥ በርካታ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

- እንደዚሁም ባለፉት ሁለት ዓመታት እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሰጠውን የመቶ ዓመት ራዕይ እውን ለማድረግ ከተቋቋሙት ግብረ ሃይሎች መካከል አንዱ የሆነውን የወንጌል ሥርጭት ግብረ ሃይልን በመምራት የኢትዮጵያ ብሄራዊ የወንጌል ምክርቤት /ኤኔክ/ እንዲቋቋም ዶ/ር ብርሃኑ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

- ዶ/ር ብርሃኑ ከነበሩበት ከፍተኛ የአካዳሚክ ተቋም ሃላፊነት ውስጥ ሳሉ እግዚአብሔር ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ስለጠራቸው የመጣው ጥሪ ግልፅ ስለነበር ያለምንም ማመንታት ለሃያአንድ ዓመታት የቆዩበትን የህክምና ሙያ ሙሉ ለሙሉ ትተው ከሚያዝያ 1/1988 ዓ/ም ጀምሮ በመንፈሳዊ አገልግሎት ተሰማርተዋል። የአገልግሎታቸው ዋና ትኩረት መሪዎችን እና አገልጋዮችን ለማሰልጠን አብያተክርስቲያናትን ትጋትና ማስተዋል ለሰፈነበት የወንጌል ስርጭት እና ደቀመዛሙርትን የማፍራት እንቅስቃሴ ማስታጠቅ ነው። ለአዲሱ አገልግሎት ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ለመውጣት ከወሰኑ በኀላ የህክምናውን ሥራ ለማቆም ሁለት ወር ሲቀራቸው እግዚአብሔር ያሳያቸውን የአገልግሎት አቅጣጫና የደረሱበትን ውሳኔ ለአዲስ አበባ ብርሃነ ወንጌል ቤ/ክ የሽማግሌዎች ጉባኤ በዝርዝር አስረድተው ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ የጉባኤውን ምክር እና የፀሎት ድጋፍ ጠይቀዋል። የሽማግሌዎች ጉባኤም ጉዳዩን በጥሞና ካዳመጠ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት የደስታ እምባን በማፍሰስ እና ለእግዚአብሔር ምስጋናን በማቅረብ ለወንድማችን ቀኝ እጃቸውን ሰጥተዋል። በዚሁም መሰረት ዶ/ር ብርሃኑ ኤክሌሽያ ተነሽ በሚል ስያሜ የጀመሩት አገልግሎት ቤተክርስቲያኒቱ ተቀብላ ሰኔ 10/1991 ዓ/ም በፀሎት ለአገልግሎቱ በመለየት አሰማርታቸዋለች። አገልግሎታቸውንም ለብርሃነ ወንጌል ቤ/ክ ተጠያቂ በሆነ መልኩ አደራጅተው እስከ ዕለተሞታቸው ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

- ደ/ር ብርሃኑ ለዚህ አገልግሎታቸው ይበልጡን ለመዘጋጀት የሥነመለኮት ትምህርት ተከታትለው በባችለር ኦፍ ቲኦሎጂ ዲግሪ አግኝተዋል። በኤክሌሽያ ተነሽ አገልግሎት የወንጌልን እና ደቀመዛሙርትን የማሳደግ አገልግሎት በአገር ውስጥ በሁሉም ክልሎች ውስጥ በተለያዩ ቤተእምነቶች ለሚገኙ ምዕመናን እና አገልጋዮች፤ በአፍሪካ፤ በአውሮፖ እና በአሜሪካ ለሚገኙ የተለያዩ አብያተክርስቲያናት ትምህርት እና ሥልጠና ሰርተዋል። ለዚህም አገልግሎት ይረዳ ዘንድ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ለሰልጣኞች እና ለአብያተክርስቲያናት ወገኖች አሰራጭተዋል። የወንጌል እና የደቀመዝሙሣ አገልግሎቱን በቋሚ እና በተደራጀ መልኩ ለማስተማር ያመች ዘንድ ልዩ ልዩ አጫጭር ኮርሶች በአዳሪነት ደረጃ በሙሉ ጊዜ ሊማሩ ለሚፈቅዱ ጢራኖስ የደቀመዝሙርነት ት/ቤት የተሰኘ የሥልጠና ማዕከል

አደራጅተው እና ተማሪዎችን ተቀብለው ትምህርት የሚሰጥበትን መርሃ ግብር ተግባራዊ አድርገዋል።

- ዶ/ር ብርሃኑ በሚሰጡት የወንጌል እና የደቀመዝሙር አገልግሎት ሣይገቱ በልዩ ልዩ የኑሮ ጉስቁልና ለሚገኙ አቅመደካሞች እና ድሆች በነበራቸው የመርዳት እና የማቋቋም ሸክም ከውድ ባለቤታቸው ከሲስተር አልማዝ ታረቀኝ ጋር ራዕያቸውን በማቀናጀት የምስራች ለድሆች የተሰኘ ፕሮጀክት ቀርፀውና ሥራውን የሚመራ ቦርድ አቋቁመው ለተግባራዊነቱ በመትጋት ላይ ነበሩ።

## የጋብቻ አቋም

- ዶ/ር ብርሀኑ ሀብቴ ከባለቤታቸው ከሲስተር አልማዝ ታረቀኝ ጋር ሐምሌ 10/1975 ዓ/ም በቅዱስ ጋብቻ ተጣምረው ለሃያአምስት አመታት በቆዩበት የትዳር ዘመን ሁለት ሴት ልጆች አፍርተዋል።

- ዶ/ር ብርሀኑ ጠንቃቃ፤ ትጉ እና ጠንካራ የቤተክርስቲያን መሪ እና አገልጋይ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ስለ አጥቢያ ቤ/ክ ህልውና እና ስለ ቅዱሳን ሕብረት ጠንካራ አቋም እና ተሳትፎ ነበራቸው። እንደዚሁም ሰዎችን ሁሉ በተለይም ክርስቲያን ወገኖችን ሁሉ የሚያፈቅሩ እና የሚያከብሩ የደከሙትን የሚያበረቱ፤ ያዘኑትን የሚያፅናኑ አስፈላጊ የሆነውን ትምህርትና ምክር ለሚያስፈልጋቸው የሚሰጡ ለአመኑበት ዓላማ እስከመጨረሻው የሚታገሉ እና ውጤት የሚያመጡ፤ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ፤ ጌታንም የሚፈሩ ምሳሌያዊ ወንድም ነበሩ።

- ዶ/ር ብርሀኑ የካቲት 7/2000 ዓ/ም ለአገልግሎት በራሳቸው መኪና ወደቡታጅራ እየተጓዙ ሳለ በድንገተኛ መኪና አደጋ በተወለዱ በሃምሳ ስድስት ዓመታቸው ወደአገለገሉት እና ወደሚናፍቁት ጌታ ሄደዋል።

- የወንድማች በስጋ ከኛ መለየት ለቤተሰባቸው፤ ለወዳጆቻቸው እና ለኢትዮጵያ ቤ/ክ ትልቅ ሀዘን ቢሆንም እግዚአብሔር ለሁሉም በተለይም ለባለቤታቸው እና ለልጆቻቸው መጽናናትን እና ብርታትን እንዲሰጣቸው የሁላችን ፀሎት ነው።